ጸጋውና የአማኞች በክርስቶስ መገለጥ ፊት መኖር

ቲቶ 2፥11-15

11፥ ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤

12-13፥ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናልና፤

14፥ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።

15፥ ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ።

በዚህ ክፍል ትልልቅ የአስተምህሮና የስነ መለኮት ቃላትና አሳቦች በብዛት ይገኛሉ። ይህንን ክፍል ስንማር እነዚህን ቃላትና አሳቦች በመፍታትም ጭምር ማየት የተገባ ነው። ቃላቱ ብዙ ናቸው፤ መዳን፥ ጸጋ፥ ኃጢአተኝነት፥ ዓለማዊ ምኞት፥ የተባረከው ተስፋ፥ ታላቁ አምላካችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፥ የክብሩ መገለጥ፥ መጠበቅ፥ ራስን መግዛት፥ ጽድቅ፥ እግዚአብሔርን መምሰል፥ በዚህ ዘመን መኖር፥ መድኃኒት፣ መቤዠት፥ ገንዘብ መሆን፥ መንጻት፥ ነፍስን መስጠት። እነዚህ ትልልቅና የታመቁ ቃላትና አሳቦች ናቸው።

ቲቶ 2፥11 ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤

ሰዎችን <u>ሁሉ</u> የሚያድን ሲል ሰዎች ሁሉ ይድናሉ ማለት ነው? አይደለም፤ ሁሉም አይድኑም። ሁሉ ይድኑ ዘንድ ግን እግዚአብሔር ይወድዳል፤ ይታገሣልም። ይውደድ እንጂ፥ ይታገሥ እንጂ ሁሉ ሁሉ ግን አይድኑም። ሁሉም አይዳኑ እንጂ ጸጋው ግን ሰዎችን ሁሉ ማዳን ይችላል፥ መዳንን ለሚወድዱ ሁሉ ጸጋው የተሰጠና የተገለጠ ነው። ሰዎችን ሁሉ የሚያድን ማለት የሚድኑትን ሰዎች ሁሉ የሚያድን ጸጋ መሆኑን አመልካች ነው። ስለ ጸጋው ነው ዋናው አሳብ።

ይህ ጸጋ <u>የሚያድን</u> ነው። መዳን የሰው ከሞት ወደ ሕይወት መሻገር ነው። ከዘላለም ኩነኔ ወደ ዘላለም ብጽዕና ማለፍ ነው። መዳን እግዚአብሔር አስቀድሞ ለሰው ልጆች ወዳቀደው የኅብረት ኑሮ መግባት ነው። ሰው በኃጢአት ከወደቀ በኋላ ከእግዚአብሔር ተለየ። እግዚአብሔር ባለበት ኃጢአት መሆን ስለማይችል፥ ሰው ደግሞ ኃጢአተኛ ስለሆነ እግዚአብሔርና ሰው ተለያዩ። ሰው የእግዚአብሔር ቁጣ ወይም ፍርድ ወደቀበትና የቁጣ ልጅ ተባለ፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ አዳነን። ኤፌ. 2፥3-5 ይህንን እንዲህ ይገልጠዋል፤ *በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ <u>በጸጋ ድናችኋልና።</u>* ይህ ነው የሚያድነው ጸጋ።

ሁሉ የሚድኑበት መንገድ ደግሞ <u>ጸጋ</u> ነው። ከላይ ባየነው በኤፌ. 2፥8-9 ላይ፥ *ጸጋው በእምነት ሉድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።* ይላል። ጸጋ ሁሉ የሚድኑበት መንገድ ነው። ከፊሉ በጸጋ ድነው ገሚሱ ደግሞ በሥራ ይድናሉ አልተባለም። ሁሉ የሚድኑት በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ሰዎችን የሚያድነው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው። መዳን በጸጋ ነው። ጸጋ ሠርተን፥ ለፍተን፥ ማስነን፥ ደክመን፥ ከፍለን የምናገኘው ነገር ሳይሆን የዚያን ነገር ተቃራኒ የሚያሳስብ ቃል ነው። ሳንሠራ፥ ሳንለፋ፥ ሳንማስን፥ ሳንደክም፥ ሳንከፍል፥ እንዲያው በነጻ የምናገኘውን፥ የሚሰጠንን ወይም የተሰጠንን ቸርነት የሚያሳይ ቃል ነው።

ጸጋው ባለቤት አለው፤ ባለቤቱም <u>እግዚአብሔር</u> ነው፤ ጸጋው የእግዚአብሔር ነው። ደግሞም <u>የተገለጠ</u> ጸጋ ነው። ጸጋው የተገለጠ ነው፤ የተገለጠውም በክርስቶስ ነው፤ ክርስቶስ በሥጋ ባይመጣ ጸጋ አይገለጥም ነበር። ጸጋ ተገለጠ፤ ጸጋ የተገለጠው በክርስቶስ *ሥጋ* ሆኖ መምጣት ነው፤ *እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናልና* ሕግ *በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።* ዮሐ. 1፥16-17። የመጽደቃችን ምክንያት እርሱ ነው፤ *በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።* ሮሜ 3፥24። ይህ ጸጋ የተገለጠው ክርስቶስ ሲገለጥ ነው።

ጸጋ ከመሰጠቱ በፊት ምን ነበረ? የድነትና የኅብረት መንገድ ምን ነበረ? ሕግ ነበር። ይህ ደግሞ ከባድ ጫና ነበረ። ማንም ሕጉን ጠብቆም እንኳ እርግጠኛ ሊሆን የማይችልበት፥ በፍርሃትና በሰቀቀን የሚኖሩበት፥ መቅረብ ጭንቅ የሆነበት ሥርዓት ነበረ። ሕጉን ሁሉ ጠብቆ የነበረና በመጠበቁ እርግጠኛ የሆነ አንድ ወጣት ወደ ጌታ መጥቶ የጠየቀው ጥያቄ ነበረ፤ *መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ?* ብሎ ጠየቀ፤ ማቴ 19፥16። ጸጋ እርግጠኛ ያደርገናል።

ጸጋ የአዲስ ኪዳን ቃል ነው። በብሉይ ኪዳን ጸጋ የሚለውን ቃል አናገኝም። በዚህ በ1954ቱ ትርጉም ውስጥ በብሉይ ኪዳን ጸጋ የሚለውን ቃል አንዴ ብቻ ሚል. 1፥9 ላይ እናገኘዋለን። እዚያ የተጻፈው חָנָן ኻናን የተባለው ቃል በሌሎች ብዙ ቦታዎች ተጽፏል፤ በየተጻፈባቸው ቦታዎች ግን የተለያዩ አሳቦች ናቸው የተላለፉት፤ እነዚህም፥ መስጠት፥ ቸርነት ማድረግ፥ ማማጠን፥ መባረክ፥ ይቅር ማለት፥ መራራት፥ መማር ወይም ምሕረት ማድረግ፥ መለመን፥ ማቆላመጥ፥ ማዘን፥ ሞገስ ማግኘት፥ አንድ ቦታ ማጓራት ይለዋል (ኤር. 22፥23) ማዘን ወይም አዝኖ ማልቀስ፥ ማከበር፥ በሚሉ የተለያዩ ቃላት ተጠቅሰዋል።

ወደ አዲስ ኪዳኑ ቃል ስንመጣ ይህ ጸጋ እነዚህን ነገሮች ሁሉ የያዘ የታጨቀ ቃል ነው። ከእግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለኛ የሆነውን መስጠቱን፥ ቸርነቱን፥ መባረኩን፥ ይቅር ማለቱን፥ መራራቱን፥ መማሩን ወይም ምሕረት ማድረጉን፥ ኃጢአታችን መወገዱን፥ የመዳን መንገድ ወለል ብሎ መከፈቱን፥ በፊቱ ሞገስ ማግኘታችንን፥ መጽደቃችንን፥ መክበራችንን ሁሉ የያዘ አንድ ቃል ነው፤ ጸጋ። የእግዚአብሔር ጸጋ። *ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና።*

ይህ ጸጋ ከማዳን ወይም ከድነት ባሻገር የሚሠራው *ሥራም* አለ። የጸጋው *ሥራ* ያለፈና ያበቃ፥ ስንድን በዳንን ቀን የተፈጸመ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከዳንን በኋላም ቀጣን ነው። የዳንነው፥ ቤዛነታችንን ያገኘነው፥ የበደላችንን ስርየት ያገኘነው በጸጋው ነው። *በውድ ልጁም፥ <u>እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥</u> በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን ለገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት።* ኤፌ. 1፥7። የዳንነው በ*ሥራችን* ሳይሆን እንዲያው በጸጋው እንደሆነው ሁሉ ከዳንን በኋላ የክርስትና ሕይወትን የምንኖረውም በበዛልን ጸጋው ነው። *<u>ጸጋውንም</u> በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን።* ኤፌ. 1፥8። ከዳንን በኋላ የሚቀጥለው ሕይወታችንም በጸጋው መሆኑን ይህ የምንመለከተው ክፍልም ይነግረናል።

ቲቶ 2፥12-13 *ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤*

ይህ ጸጋ ከማዳን ወይም ከድነት ባሻገር የሚሠራው *ሥራም* አለ። ይህ ጸጋ ያስተምረናል። ያስተምረናል ሲል ጸጋውን ልክ እንደ እግዚአብሔር ወይም እንደ ሰው ያለ ያደርገዋል። የአስተማሪ ባሕርይ ያላብሰዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ላልሆኑ አንዳንድ ነገሮች ስብእና ሲያላብስ ይታያል፤ ለምሳሌ በምሳሌ በብዙ ቦታዎች፥ በተለይ

ምሳ. 8 ላይ ጥበብ በሴት ተመስላ ቀርባለች። ስትናገር፥ ስትመክር፣ ስትመሰክር፥ ስታስጠነቅቅ ይታያል። ይህም ያንን ዓይነት ነው። ጸጋው ያስተምረናል።

ግሱ ያስተምረናል ነው። ከግሱ ጀምረን ወደ ኋላ ስንሄድ፤ ይህ ጸጋ ያስተምረናል፤

ምን ያስተምረናል? በአሁኑ ዘመን እንዴት እንድንኖር ያስተምረናል። እንዴት ነው በአሁኑ ዘመን የምንኖረው? በዚህ ስር አምስት ነገሮች ተዘርዝረዋል፤

- ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት <u>ክደን</u>፥
- የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ <u>እየጠበቅን</u>፥
- ራሳችንን <u>በመግዛትና</u>
- <u>በጽድቅ</u>
- እግዚአብሔርንም <u>በመምሰል</u>

የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ራስን በመግዛት እና በጽድቅ መኖር የሚሉትን ከዚህ በፊት ተመልክተናቸዋል። መሪ ሽማግሌዎች ጻድቅ እንዲሆኑ ያለውን በቲቶ 1፥8 ስናይ ጻድቅ ማለት ቀጥተኛ፥ ቀና፥ የፍርድ ትክክለኛ ማለት መሆኑን፥ የፍርድ ቅንነትንም እንደሚያሳይ፥ በመጀመሪያ ጻድቅ የተባለው ቃል የተነገረለት ሰው ኖኅ መሆኑን፤ ኖኅ ጻድቅ፥ ፍጹም፥ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ሰው መሆኑን፥ የእምነት ሰውና ታዛዥም እንደሆነ አይተን ጻድቅ ምን እንደሚመስል ተመልክተን ነበር።

በአዲስ ኪዳን የክርስቲያን ጽድቅ በክርስቶስ በማመን የሚገኝ ኹነት ወይም አቋም መሆኑን፥ ጽድቅ እምነትን የሚከተል የትክክለኝነት ወይም ትክክለኛ ሆኖ የመቆጠር መታወቂያ መሆኑን፥ ጻድቅ ቀና፥ ጠማማና ጠምዛዛ ያልሆነ፥ ቀጥተኛ፥ ወላዋይነት የሌለበት፥ ማለት መሆኑንም አይተን ነበር። ጸጋው በጽድቅ መኖርን ያስተምረናል ሲባል በክርስቶስ እንደ ጻደቅን ሰዎች ሆነን ትክክለኛ ኑሮን መኖርን ያስተምረናል፤ ያሳስበናል ማለት ነው። ከሞት ወደ ሕይወት በጸጋው ከመጣን፥ በሕይወት መመላለስም በጸጋው ይሆንልናል።

<u>ራስን መግዛትንም</u> በስፋት አይተነዋል። ቃሉ ለመሪ ሽማግሌዎች፥ ለአረጋውያን ሽማግሌዎች፥ ለቆነጃጅት ተነግሯል። በቀጥታም ባይሆን ለአሮጊት ሴቶችም ተነግሯል። ራስን መግዛት በቁጥጥር ስር መሆን፥ የተገሩ መሆን ነው። እንደ ባለ አእምሮ ማሰብ፥ ማስተዋል፥ ጠንቃቃ መሆን ነው። አዲስ ኪዳን ራስን ስለመግዛት ብዙ ይናገራል፤ ራስን መግዛት ከመንፈስ ፍሬ ዝርዝር ውስጥ ተጠቅሷል፤ ገላ. 5፥22። ከዚህ የምንገነዘበው፥ ራሱን የሚገዛ ሰው እርሱ ራሱ የተገዛ ሰው ነው ማለት ነው።

በመንፈስ ቅዱስ የተገዛ ሰው ነው፤ በእርሱ ቁጥጥር ስር የሆነ ማለት ነው። ለአሮጊቶች ሴቶችም በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ፤ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ ሲል፥ ለወይን ጠጅ ካልተገዙ ለሌላው ተቆጣጣሪ የሚገዝዙ ማለት ነው። ኤፌ. 5፥18 *መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤* ይላል። ይህ የሚያሳየው ሁለት ተቆጣጣሪዎችን ነው። ራስን መግዛት የመንፈስ ፍሬ ከሆነ፥ ማባከን በወይን የመሞላት ምልክት እንደሆነው ሁሉ ራስን መግዛት በመንፈሱ የመሞላት ምልክት ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሰው ዓይነተኛ ምልክት ሌላ ሳይሆን የመንፈስ ፍሬ ነው። ራስን መግዛት ለመንፈስ ቅዱስ መገዛት ነው። በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሆኖ መኖር ነው። በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በእርሱ ቁጥጥር ስር መሆን ማለት ነው። ይህንንም እንድንሆን፥ ራሳችንን እንድንገዛ ጸጋው ያስተምረናል።

እንድንኖር ያስተምረናል የተባሉትን ሌሎቹን ሦስቱን እንመልከት፤ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊን ምኞት ክደን፥ መካድ ማለት፥ 'አይደለም ወይም አይደለሁም' ማለት ነው። መካድ ሁለት የተለያዩ ትርጉሞች አሉት።

1. መካድ ማለት፥ እውነት የሆነውን እውነት አይደለም ማለት ነው። ይህንን በተለምዶ መካድ እንለዋለን እንጂ መካድ አይደለም። መዋሸት ነው። ሁለት ምሳሌ እንይ። በዘፍ. 18 <u>ሣራ</u> እንደምትወልድ ሲነገራት ሳቀች፤ ለመሳቋ ስሞታ ሲቀርብ፥ *ሣራም ሰለ ፈራች፦ አልሳቅሁም ስትል ካደች። እርሱም፦ አይደለም፥ ሳቅሽ እንጂ አላት።* ሣራ ዋሸች። ካደች ማለት ዋሸች ነው። <u>ጴጥሮስ</u> ኢየሱስን፥ 'አላውቀውም!' ሲል መካዱ ነው። በሦስቱም ተባባሪ ወንጌላት ውስጥ ታሪኩ ይገኛል። አያውቀውም? ያውቀዋል። ግን ዋሸ። ማቴ. 16፥16 ላይ፥ *አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ፤* ያለው፥ አያውቀውም? ያውቀዋል። በተለይ ማቴ. 26፥72 ላይ ያለው ቃል ይህንን ምስክርነቱን እጅግ የሚቃረን ነው፤ *ዳግመኛም ሲምል፦ ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ካደ።* ምኑን? ሰውየውን። ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ያለውን፥ ሰውየው! እሺ ሰውየውም ይበለው፣ ግን ቀጥሎ ምን አለ? አላውቀውም። አያውቀውም? ያውቀዋል፤ ስለዚህ ዋሸ።

መካድ መዋሸት ነው፤ እውነቱን እውነት አለማለት ነው። ባለፈው በቲቶ 1፥16 እንዳየነው *እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ሰለ ሆኑ፥ በሥራቸው ይክዱታል።* የተባለው በአፍ የመናገርና በተግባር ያለመኖር የግብዝነት ክህደት ነው። መዋሸት ነው።

2. ሌላው የመካድ ትርጉሙ፥ መተው፥ መራቅ፥ የኔ አይደለም፥ አልፈልገውም ማለት ነው፤ እምቢ ማለት ነው። ይህኛው መካድ የሚለው ቃል፥ ከመካድ ይልቅ መክዳት የሚለው ትክክለኛውን አሳብ ያሳያል። ጓደኞች ተከዳዱ ሲባል፥ ወይም ወላጅ ልጅን፥ ልጅ ወላጁን ከዱ ሲባል፥ የኔ አይደለም አሉ ማለት ነው። መክዳት ጥሩ ነገርንም፥ መጥፎ ነገርንም ሊሆን ይችላል። የሚከዱት ነገር ጥሩ ከሆነ ክዳቱ መጥፎ ነው።

ለምሳሌ፥ በ1ጢሞ. 4፥1-2 *መንፈስ ግን በግልጥ፦ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያደመጡ፥ ሃይማኖትን <u>ይክዳሉ</u> ይላልና* ይላል። እዚህ ይክዳሉ የተባለው ከአንድ ነገር መራቅ ነው፤ ከእምነት፥ ከሃይማኖት። መልካምን ነገር መክዳት ጉዳት ነው። ጥፋት ነው። ወይም ይሁዳ ቁ. 4 ላይ፥ *ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ አንዳንዶች ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንንና ጌታችንንም ብቻውን ያለውን አዩየሱስ ክርስቶስን <u>ይክዳሉ</u>።* ሲል ይህ መልካሙን መካድ ነው። ሐዋ. 3፥14 *እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም <u>ክዳችሁ</u> ነፍሰ ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ፥* ሲል መልካሙን አንፈልግም ማለታቸውን አመልካች ነው።

በአንጻሩ ደግሞ መጥፎውን ነገር መካድ መልካም ነው። እንዲህ ያለውን መካድ ቃሉም ያስተምራል። ለምሳሌ፥ በዕብ. 11፥24 *ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዲባል በእምነት <u>እምቢ አለ</u>፤* በሚለው ውስጥ፥ 'እምቢ አለ' የሚለው ያንን ነው። ከመካድ ጋር አንድ ነው። በሉቃ. 9፥23 *ለሁሉም እንዲህ አላቸው፦ በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን <u>ይካድ</u> መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።* ሲል ይህ መካድ ለራስ እምቢ ማለት ነው። የራስን ምኞት እምቢ ማለት ነው። እኔ የእኔ አይደለሁም ማለትም ነው።

ወደ ቲቶ 2፥12-13 ስንመጣ፥ *<u>ኃጢአተኝነትንና</u> ዓለማዊን ምኞት <u>ክደን</u>፥* የሚለው ትክክለኛ ያልሆነውን፥ መልካም ያልሆነውን፥ ከጌታ ያልሆነውን መካድ ነው። ጎጂውን፥ አምካኙን፥ ፍሬቢስ አድራጊውን፥ ከጌታ የሚያርቀውን መተው፥ መራቅ፥ የኔ አይደለም፥ አልፈልገውም ማለት ነው፤ እምቢ ማለት ነው። ኃጢአተኝነትን የሚለውን ቃል ልብ እንበል። ኃጢአትና ኃጢአተኝነት የተለያዩ ናቸው። ኃጢአት አሳቡና ድርጊቱ ነው። ኃጢአተኝነት ግን በዚያ ውስጥ የመኖር ሁኔታ ነው። ኃጢአትን ስንታገሰው፥ ዝም ስንለው እንደነዝዛለን። ከዚያ መቆርቆሩ ይተዋል፤ አብሮ መኖር፥ ደባልነት መረበሹ ያቆማል። ቀጥሎ እንዲያውም በሥጋዊነት ለሚኖሩት መመቸት ይጀምራል። ያኔ ኃጢአት ሳይሆን ኃጢአተኝነት መሠልጠን ይጀምራል። ጸጋው ያንን እንድንክድ ያስተምረናል።

ጸጋው <u>ዓለማዊ ምኞትንም</u> እንድንክድ ያስተምረናል። የዚህችን ዓለም ሸቀጥ ምኞትና ወጥመድ እንድናመልጥ ያስተምረናል። ዓለማዊ ምኞት ዓለማዊ ሰው የሚመኛቸው ነገሮች ናቸው። ዓለማውያን ሰዎች ሰማያውያን አይደሉም። አሳባቸው ምድራዊ ነው። ጳውሎስ ለፊልጵስዩስ አማኞች የመስቀሉ ጠላቶች ሆነው ስለሚመላለሱ ሰዎች ሲናገር፥ *መጨረሻቸው ጥፋት ነው፥ ሆዳቸው አምላካቸው ነው፥ ክብራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ ነው።* እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ *ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለንና፤* አለ፤ ፊል. 3፥19-20። እዚህ ንጽጽሩ ግልጽ ነው። 'እነሱ ምድራውያን ናቸው፤ እኛ

ሰማያውያን ነን ነው። አገራችን በሰማይ ነው፤ በዚህ የምትኖር ነዋሪ ከተማ የለችንም፤ ከዚያ የሚመጣ ጌታ አለን' ነው የሚለው።

በዚህች ምድር ስንኖር እንግዶችና መጻተኞች ብቻ ነን። ስንኖር እንደ እንግዶች ነው መኖር ያለብን። እነ አብርሃም እንደ እንግዶች ነበር የኖሩት። ዕብ. 11፥13-16 ስለ እንግድነታቸው አኗኗር ሲናገር፥ *እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተስፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ። እንዲህ የሚሉት ለእነርሱ የሚሆነውን አገር እንዲፈልጉ ያመለክታሉና። ያን የወጡበትን አገር አስበው ቢሆኑ፥ ሊመለሱ ጊዜ በሆነላቸው ነበር፤ አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም፥ ከተማን አዘጋጅቶላቸዋልና።* ይላል። የወጡበትን አገር አስበው፥ ናፍቀው፥ ሊመለሱ ከጅለው ቢሆኑ ጊዜ ነበራቸው ለመመለስ ጊዜ ነበራቸው፤ ዕድልም ምርጫም ነበራቸው። ግን አላደረጉም። ተጠርተው፥ ተመርተው ነው የወጡት። ላይመለሱ ድንጋይ ወርውረው እንደሚባለው ሆነው ነው የወጡት።

ዓለማዊ ምኞት ሰንነ ሊይዘን የተገባን ጉዳይ አይደለም። የተጠራንበት መጠራት የከበረ አጠራር ነው። ከዓለም የወጣነው በዓለም ብንኖርም ዓለማዊ ምኞትን ተሰናብተን ነው። ከዓለም የወጣነው በዓለም እያለን ዓለም ቤቴ አይደለችም የምንል ሆነን ነው። ወገኖች፥ በዚህች ምድር ስንኖር እንግዶች ነን፤ መጻተኞች ነን፤ መሻዳሪዎች ነን፤ አላፊ መንገደኞች ነን፤ ይህ አይጥፋን። በዓለማዊ ምኞት፥ ትተነው፥ ጥለነው በምንሄደው ነገር ተተብትበን አንኑር፤ አንቅር። እንዳንቀር ያተምረናል፤ ጸጋው።

እየጠበቅን፥ እንድንኖር ያስተምረናል። ምን እየጠበቅን? *የተባረከውን ተስፋችንን አርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን።* በዚህ ውስጥ ጥቂት ነጥቦችን እንይ፤

ይህ ነገር *የተባረከ ተስፋ* ተብሎአል። ተስፋ ምኞት አይደለም። ምኞት ሊፈጸምም ላይፈጸምም ይችላል። ተስፋ ግን ተፈጻሚ ነገር ነው። ተስፋ ካልተፈጸመ ተስፋ ሰጪው የታመነ ስላልሆነ ነው። እግዚአብሔር ደግሞ የታመነ ነው። ይህ ነገር ተስፋ ነው፤ ተፈጻሚ ነገር ነው። ተስፋ ብቻ ሳይሆን የተባረከ ተስፋ ነው። ብጽዕና ያለበት ተስፋ ነው፤ ይህ ተስፋ የጌታ መገለጥ ነው። የተባረከ የሆነበት ምክንያቱ መምጣቱ፥ በክብር መገለጡ ልንደርስበት ወደታሰበልን ዘላለማዊ ማንነትና ስፍራ የሚያደርሰን መንገድ በመሆኑ ነው።

የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን። ይህ ስለ ጌታ፥ ስለ ክርስቶስ የሚናገር ክፍል ነው። ጌታ ምን ተብሎ

ተጠቀሰ? *ታላቁ አምላካችን እና መድኃኒታችን*። ግሱ የአንድ ባለቤት ግስ ነው። ስለዚህ *ታላቁ አምላክ እና መድኃኒቱ* ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህ ክፍል የኢየሱስን አምላክነት በግልጥ የሚናገር እውነት ነው።

የታላቁን የአምላካችንን፤ ኢየሱስ ነው *ታላቁ አምላክ* የተባለው። የኢየሱስ አምላክነት ሰዎች ያቀዳጁት አምላክነት አይደለም። ኢየሱስ ራሱ አምላክ ነው እንጂ በሰዎች አልመለኮተም። ማንም ሰው በሌሎች አምላክ አይደረግም፤ ሊሆን ስለማይችል። ሰዎች ሰዎችን ሊያመልኩ ይችላሉ እንጂ ሊያመለኩቱ አይችሉም። እንደ ጣዖት ሊያመልኩ ይችላሉ፤ ጣዖት ግን አምላክነት የለውም። ይመለካል እንጂ አምላክ አይደለም። ሰዎች ስለሚያመልኩት አምላክ ይባላል እንጂ አምላክነት ወይም መለኮትነት የለውም።

<u>ኢየሱስ በራሱ አምላክ ነው እንጂ በሰዎች አምላክ አልተደረገም።</u> ሰዎች በአምላክ ይፈጠራሉ እንጂ ሰዎች አምላክን አይፈጥሩም። ሰዎች ምንም ነገር መፍጠር አይችሉም። እንዲያው ቻሉ ቢባል እንኳ፥ ከራሳቸው የሚበልጥን ምንም ነገር አይፈጥሩም። አምላክ ከሰው እንደሚበልጥ የታወቀ ነው። አምላክ፥ እውነተኛ አምላክ አንድ ብቻ ነው። ዮሐንስ ይህንን እውነተኛ አምላክ ሲገልጠው እንዲህ አለ፤ 1ዮሐ. 5፥ 20 *የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥ እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።* ያደረጋቸው

በ1ተሰ. 1፥9-10 *እነርሱ ራሳቸው ወደ እናንተ መግባታችን እንዴት እንደነበረ ስለ እኛ ይናገራሉና፤ ለሕያውና ለእውነተኛ አምላክም ታገለግሉ ዘንድ፥ ከሙታንም ያስነሳውን ልጁን እርሱንም ኢየሱስን ከሚመጣው ቍጣ የሚያድነንን ከሰማይ ትጠብቁ ዘንድ፥ ከጣዖቶች ወደ እግዚአብሔር እንዴት ዘወር እንዳላችሁ ይናገራሉ።* እውነተኛውን አምላክ ማገልገል ብቻ ሳይሆን፥ መጠበቅንም እንዲጠብቁ እውነተኛ ካልሆኑ አማልክት ወይም ጣዖታት እንዴት ዘወር እንዳሉ ይናገራል።

<u>ኢየሱስን ያደረጋቸው ተአምራትና ምልክቶችም አምላክ አላደረጉትም፤</u> ምክንያቱም፥ ተአምራት በሰዎችም በእግዚአብሔር ፈቃድ ይደረጋሉ፤ በኢጋንንታዊ አሠራርም ይደረጋሉ። የኢየሱስ *ታላቅ አምላክነት* የማንነቱ አምላክነት እንጂ የተቀበለው፥ የተሰጠው አምላክነት አይደለም። ዮሐ. 1፥1-2 ይህንን ነው የሚያስረዳን። እርሱ በመጀመሪያ የነበረው አምላክ ነው። ስለዚህ *ታላቁ አምላክ* ነው።

<u>*የመድኃኒታችንን፤*</u> ኢየሱስ መድኃኒት ነው። ስሙ ኢየሱስ መድኃኒት ማለት ነው። *ልጅም ትወልዳለች፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።* ማቴ. 1፥21። ኢየሱስ አዳኝ ነው፤ እንደ ስሙ። ከሌሎች የሥጋ ደዌ ማዳን አይደለም፤ ያንን እግዚአብሔር በማንም አማካይነት ሊያደርግ ይችላል። *ሕዝቡን*

ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ። የተባለውን ግን፥ ከኃጢአት ማዳንን ግን በሌላ በማንም ሊያደርግ አይችልም እንድንበት ዘን የተሰጠ ሌላ ስም የለም፤ ሐዋ. 4፥12፤ *መዳንም በሌላ በማንም የለምና፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።* ኢየሱስ መድኃኒታችን ነው።

ክብር መገለጥ እየጠበቅን፤ የእርሱን ክብር መገለጥ መጠበቅ አኗኗራችንን ጤናማ ያደርገዋል። ጥበቃ በአጠቃላይ አኗኗር ላይ የሚቀይረው ነገር አለው። በሆነ ምክንያት አንድ አዲጋ ይደርሳል የሚል ትንበያ ቢኖር፥ ለምሳሌ፥ ጎርፍ ይመጣል፥ ድርቅ ይሆናል፥ የእህል እጥረት ይከሰታል ከተባለ፥ ያ ነገር ከመምጣቱ በፊት በቂ ዝግጅት እናደርጋለን። የሆነ ዝግጅት ከፊታችን ካለ፥ ሠርግ፥ ወይም ምረቃ፥ ወይም የሚከበር በዓል ካለ የዚያ ነገር ጥበቃችን ወይም አጠባበቃችን በአኗኗራችን ላይ ለውጥ ያመጣል። እንግዳ ቤታችን እንደሚመጣ ካወቅን ተዝረክርከን አንጠብቅም። እነዚህ ሁሉ መቼ እንደሚሆኑ የምናውቃቸው ነገሮች ናቸው።

የጌታ መምጣት ደግሞ እንደሚሆን እንጂ መቼ እንደሚሆን የማናውቀው ነገር ነው። እንግዳ ወደ ቤታችን ሲመጣ ወይም አንድ የአገር መሪ ሊጎበኝ ሲመጣ የሚመጣበት ቀንና ሰዓት ይታወቃል፤ ከጥቂት ሰዓቶች ወይም ቀናት በፊት በፊት የአቀባበል ዝግጅቱ ተደርጎ ይጠናቀቃል። ግን ድንገት የሚመጣ ከሆነ ሁሌ ዝግጁ ሆኖ መጠበቅን ይጠይቃል። የመሥሪያ ቤት አለቃ በድንገት ወደ ሠራተኞች ሲመጣ ዝርክርኩቹ ይርበተበታሉ፥ ይተራመሳሉ። ከሥራ ገበታቸው ሌላ ጉዳይ ላይ የሆኑ ሰዎች ድንገት እጅ ከፍንጅ ሲያዙ ያፍራሉ። ግን በታማኝነት በመስኩ ላይ የተሰማሩት ማንም መቼም ቢመጣ ድንገት አይሆንባቸውም፤ ድንጋጤም አይሆንባቸውም።ጌታ እንደሚመጣ እናውቃለን፤ የቀጠሮው ቀን ግን የሚታወቅ አይደለም። ያኔ ነው ትክክለኛ የጥበቃ አኗኗር የሚታየው። ቀኑን ብናውቅ ቀኑ እስኪቀርብ፥ እስኪጠጋ ብዙም ላንሰናዳ እንችላለን፤ እንዲያውም ዝርክርክ ልንሆን እንችላለን። የማይታወቅ ቀን ግን ሁሌ ዝግጁ አድራጊ ጉዳይ ነው። የጌታ መምጣት ጥበቃ ልክ እንደዚያ ነው።

የተባረከውን ተስፋችንን የጌታን በክብር መገለጥ እንድንጠብቅ ተነግሮናል። መቼ እንደሚመጣ አናውቅም። እንደሚመጣ፥ በክብር እንደሚገለጥ ግን እናውቃለን። ይህ ያነበብኩት አንድ ታሪክ ነው። በግሪክ አገር የሚገኝ አንድ ደሴት ላይ ትልቅ የተንጣለለ የሚያምር ግቢ አለ፤ ጎብኚዎች በዚያ ሲያልፉ የግቢውን ውበት፥ የሳሩን ማማር፥ የአትክልቶቹን መከርከም፥ የዛፎቹን ውበት፥ ጽዳቱን እያደነቁ አትክልተኛው ሲከረክም አግኝተው ስለ ግቢው ጠየቁት። የማን ግቢ ነው? ባለቤቱ ማን ነው? የት ነው ያለው? . . . ሰውየው ባለቤቱን በስም እና በፎቶ ብቻ ነው እንጂ አያውቀውም። ሥራ ከጀመረ ጀምሮም መጥቶ አያውቅም። ከጠያቂዎቹ አንዱ እጅግ ተገርሞ፥ 'ታዲያ እኮ የግቢው ጽዳትና የአትክልቱ አጠባበቅህ ባለቤቱ ልክ ነገ የሚመጣ ነው የሚመስለው።' ሲለው፥ አትክልተኛው፥ 'ተሳሳትክ፤ ነገ ሳይሆን ዛሬ፥ እንዲያውም፥ አሁኑኑ እንደሚመጣ አድርጌ ነው የምጠብቀው።' አለው። ነገ ሳይሆን ዛሬ፥ አሁኑኑ።

ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው፤ ሉቃ. 12፥ 37።

ይህ ጸጋ ሦስቱንም የጊዜ ክልሎች ሁሉ ያቀፈ ነው። ከደን - ኃላፊ ጊዜ፤ እየጠበቅን - ከአሁን ጀምሮ ወደፊት፤ በአሁኑ ጊዜ - አሁን።

ሲተጉ የሚያገኛቸው ሲመጣ ጌታቸው / በመክሊታቸው የሠሩ ምስጋና አላቸው / አገልግሎቱን ያልናቀ በጥቂቱ ታምኖ / ብድራቱን ይቀበላል ሥራው ተተምኖ። ጥበቃ ጥንቃቄን ይወልዳል። ዕለት ዕለት መሰናዳትን ይወልዳል። ዕለት ዕለት እርሱን በመምሰል መኖርን ይወልዳል።

<u>እግዚአብሔርንም በመምሰል፤</u> እግዚአብሔርን መምሰል የሚለውን ቃል በአዲስ ኪዳን የተጠቀሙት ጳውሎስና ጴጥሮስ ናቸው። በብዛት የጠቀሰው ጳውሎስ ነው፤ ከጠቀሰውም በብዛት የሚገኘው 1ጢሞቴዎስ ውስጥ ነው። እግዚአብሔርን መምሰል ማለት እግዚአብሔርን መፈለግ፥ እርሱን መከታተል፥ አምልኮት፥ አክብሮት፥ መንፈሳዊነት፥ ቅድስና ነው። እግዚአብሔርን መምሰል የሰው ሁለንተናው ነው፤ ሲፈጠርም በአምሳሉ፥ በምስሉ፥ በምሳሌው ነዋ የተፈጠረው። የተፈጠረው ለግንኙነት፥ ለኅብረት ነው። እግዚአብሔርን መምሰል ወደ እግዚአብሔርነት ማደግ ወይም ምልኩትና አይደለም። እኛ አንመለኩትም፤ ስንፈጠር ሰዎች ነን፤ ስንኖርም ሰዎች ነን፤ ስንሞትም ሰዎች ነን፤ ከሞት በኋላ በትንሣኤም ሰዎች ሆነን እንቀጥላለን። መምሰል ግን በዚህ ሰውነታችን፥ በዚህ ሰው መሆናችን ውስጥ የእርሱ ባሕርይ ሲንጸባረቅ ማለት ነው። ለምሳሌ፥ ሰውን መውደዱን ስንመስል፥ መራራቱን ስንመስል፥ ቅዱስነቱን ለመምሰል ስንከታተለው፥ በፍለጋው ስንሄድ እርሱን መምሰላችን ነው።

ክርስቶስን መምሰል ደግሞ የተጠራንበት መጠራታችን ነው። ሮሜ 8፥29 ያንን ይለናል፤ *ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና።* ይህ የአብ ውሳኔ ነው። እግዚአብሔርን መምሰልን እንናፍቅ ዘንድ የምንመስለው ክርስቶስ ተሰጠን። ክርስቶስን መምሰል ተነገረን። መምሰልም በጸጋው ነው። ጸጋው ምንን ያስተምረናል? እግዚአብሔርን በመምሰል እንድንኖር ያስተምረናል።

<u>በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል፤</u> በዚህ አሁን ባለንበት ዘመን፤ በሚመጣው አይደለም። እነዚህ ከላይ ያየናቸው መንፈሳዊ የአመላለስ ልምምዶች እዚያ ስንሄድ፥ ፍጹማን ስንሆን፥ ስንከብር ሳይሆን እዚህና አሁንም እንድንለማመዳቸው ጸጋው የሚያስተምረን ልምምዶች ናቸው።

ቲቶ 2፥14 መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአልና።

ቁጥር 14 ከመምጣቱ ጋር የተያያዘውን ነገር ያስረዳል፤ ታላቁን ተስፋችንን የምንጠብቅበት ምክንያት ቀድሞ የተደረገልን ነገር መኖሩን በማሳየት ነው። በመጀመሪያ መድኃኒታችን የተባለው ከላይ *የታላቁን* የአምላካችንንና *የመድኃኒታችንን* ስንል ያየነው መድኃኒት ነው። እርሱም ኢየሱስ ነው።

እርሱ ምን አደረገ? *ነፍሱን ሰጠ።* ትልቁ የሰው መሆን ዋጋ ነው ነፍስን መስጠት። ለሰው ሊከፍለው የሚችለው ሌላው ሁሉ ነገር ከነፍስ ያነሰ ዋጋ ነው። ነፍስ ግን ከሁሉ የበለጠው ትልቁና ብቸኛው ዋጋ ነው። ጌታ በሥጋ ሲገለጥ፥ ሰው ሲሆን ይህን ያደረገው ትልቁን ዋጋ ለመክፈል ነው። የከፈለውም በመስቀል ላይ ቤዛ ሆኖልን ነው።

ነፍሱን ሰጠ። ለምን ሰጠ? ለሁለት ነገሮች ሰጠ፤ 1. እንዲቤዠን፥ እና 2. እንዲያነጻ።

እንዲቤዠን፥ መቤዠት ዋጋ ከፍሎ ከጥፋት ማዳን ነው። ቢተውት፥ ዝም ቢሉት የሚጠፋ ነገርን ዋጋ ከፍሎ *መታደግ፥* ከጥፋት ማዳን ነው። *መዋጀት* ነው። 1ጴጥ. 1፥ 18-19 *ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር በብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፥ ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ደም በክቡር የክርስቶስ ደም <u>እንደ ተዋጃችሁ</u> ታውቃላችሁና።* ይላል። ከከንቱ ኑሮ በብርና በወርቅ መዋጀት ራሱ ትልቅ ውለታ አለበት። በክቡር የክርስቶስ ደም መውዋጀት ግን ቀጣዩን ኑሮ ለእርሱ ለመስጠት *መሥዋዕት* የሚያስደርግ ነው። በቤዠት ወይም *መዋጀት* ዋጋ ከፍሎ ከጥፋት ማዳን፥ *መታደግ* ነው።

እንዲቤዠን፥ ከምን? ከዓመጽ። ዓመጽ የኃጢአት ሌላ ስም ነው። ሕግ የለሽነት፥ ወይም ሕግ ቢኖርም ሕግን ተላላፊነት ነው።

እንዲያነጻ፥ ማንን? መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ። በመጀመሪያ ይህ ሕዝብ የሚነጻው እንዲያው ለመንጻት ብቻ አይደለም። ለአንድ ባለቤት ነው፤ የሚነጻውም ራሱ ባለቤቱ ነው። የሚያነጻው እራሱ ነው፤ ለራሱ ነው። ያንን ለማድረግ ነው ራሱን የሰጠው። ይህ ሕዝብ ደግሞ በሁለት መገለጫዎች ተገልጧል፤ *መልካም ለማድረግ የሚቀና፥* እና *ገንዘቡ የሚሆን* ተብሏል። መልካም ማድረግ እስካሁን ቲቶ 1 እና 2ን ስናይ ያየናቸው ከክርስቲያኖቹ የሚጠበቁት በጎ ነገሮች ናቸው። ገንዘቡ የሚሆን የሚለው ቃል ልዩ መሆንን የሚናገር ነው። ልዩ

ሕዝብ፤ ከመደዳነት፥ ከተርታነት የወጣ የተለየ፥ የከበረ፥ ክቡር፥ ዋጋ የተከፈለበት፥ ደም የፈሰሰለትና በደም የተዋጀ ሕዝብ፥ ያንን የሚያሳይ ቃል ነው። ለዚህ ነው ጌታ ነፍሱን የሰጠው።

ይህንን ሲል ጳውሎስ በንድፈ አሳብ ደረጃ ብቻ እየተናገረ አለመሆኑን ልብ እንበል። ያለፈ፥ የቀደመ ታሪክን ብቻ እንደ ታሪክ እየተናገረ ሳይሆን ራሱንና የቀርጤስን ክርስቲያኖችም ጨምሮ፥ እስሌቱ ውስጥ አስገብቶ መሆኑን እናስተውል። *መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ስለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።* ሲል መድኃኒታችን፥ የኛ መድኃኒት፥ የኛ አዳኝ ማለቱ ነው። እንዲቤዠን ሲል፥ እኛን እንዲዋጀን ማለቱ ነው፤ ራሱንም የቀርጤስ ቅዱሳንንም ጨምሮ ነው። ያ ያኔ ብቻ አይደለም። ዛሬም፥ እዚህም እውነት ነው። ይህ የምናጠናው ቃል ያ እዚያ የተነገረው ቃል ነው፤ ይህ እውነት ነው። ግን ያና እዚያ ብቻ ሳይሆን አሁንና እዚህም የሚናገር፥ የሚያስተምር፥ የሚገናዘብ ቃል ነው። ቃሉ በጊዜና በቦታ ላሉ ቅዱሳን ሲጻፍ እኛም ታሳቢ ተደርገን የተጻፈ ቃል ነው።

ጌታ ነፍሱን የሰጠው እኛን ሊቤዥ ነው፤ እኛን ገንዘቡ ወይም ልዩ ሕዝብ ሊያደርግ ነው። እኛ ተራ ወይም ተርታ ሰዎች ነን። ግን ከተርታ በላይ የሆንን ሰዎችም ነን። ዋጋ የተከፈለልን ሰዎች ነን፤ የከበርን ሰዎች ነን። ገንዘቡ ያደረገን ከገንዘብ በላይ የሆነ ዋጋ ከፍሎ ነው። በዓይኖቹ ፊት ክቡራን ነን። ራሳችንን ዝቅ አድርገን እንድናይ የሚያደርጉን ሰዎች ወይም ነገሮች ሲገጥሙን ይህንን የከበርን መሆናችንን የሚያሳየንን እውነት እናስብ። ክቡር ዋጋ የተከፈለልን ሰዎች መሆናችንን።

ገና በመጀመሪያ ላኪውንና ተቀባዩን ስንመለከት ይህንን አይተን ነበር። እግዚአብሔር እኛን የመረጠን የምርጫ መስፈርቱን ለኛ ሲል ዝቅ አድርጎልን ሳይሆን ዋጋውን ሙሉ በሙሉ ከፍሎ ነው ብለን ነበር። የጳውሎስን ባሪያነት ስናይ እኛም በክቡር ዋጋ የተገዝዛን ሰዎች ነንና ሁለት ነገሮች ልብ እንበል በማለት፥

1ኛ፥ የከበርን ነን፤ ዋጋችን ክቡርነታችንን ይመሰክራል። እላያችን የተለጠፈው ዋጋ ወይም price tag የክርስቶስ ደም ነው። ስለዚህ እኔ ውድ ነኝ፤ እኔ ክቡር ነኝ እንበል። ክቡራን ነንና ማንም ዝቅ አያድርገን።

2ኛ፥ ባለቤት አለን። እኛ የኛ አይደለንም። እኛ በኛ ላይ ሥልጣን የለንም። እኛ የኛ ጌታ አይደለንም። ሌላ ማንም በኛ ላይ አለአግባብ መሠልጠን የለበትም። ባለቤት አለን፥ ጌታ አለን። ገንዘባችን፥ ጊዜያችን፥ ቁንጅናችን፥ ጉልበታችን፥ አእምሮአችን፥ ሰውነታችን፥ የኛ አይደለም፤ የጌታ ነው። በነፍስ የተገዛን ነንና ባለቤት አለንና ከእርሱ ሌላ ማንም አይግዛን። ይህ እውነት ነው።

ቲቶ 2፥15 *ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር ገሥጽም፤ ማንም ሊይናቅህ።*

<u>ተናገር፤</u> ምን ተናገር? ይህን ከላይ ጳውሎስ የጻፈለትን እውነት። መናገር ብቻ አይደለም፤ ሲናገር የሚናገርበት አነጋገርም ሊስተዋል የተገባው ነው። *በሙሉ ሥልጣን፤* እንደ ጳውሎስ እንደራሴ፥ ወይም እንደ ጳውሎስ እንደራሱ ሆኖ እንደሚያገለግል አገልጋይ፥ እንደ ክርስቶስ ወኪል፥ ሥልጣን እንደተቀበለ፥ ትእዛዝ እንደተሰጠው ሰው ሆኖ እንዲናገር ነገረው።

<u>ምከር፤</u> ምከር የሚለውን ቃል እዚሁ ቲቶ ውስጥ ሁለቴ አይተነዋል፤ አንዴ ለሽማግሌዎች ቲቶ 1፥9 ላይ፥ *ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅሰ ይችል ዘንድ፥ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና።* ባለበት ቅዱሳንን መምከርን ያሳያል። ሌላው ቲቶ 2፥6 ላይ፥ *ጎበዞችም እንዲሁ ራሳቸውን እንዲገዙ ምከራቸው።* ባለበት ቲቶ ወጣቶችን እንዲመክር በተነገረበት የተጻፈ ነው። እዚህም ቲቶን ነው እየተናገረ ያለው። ትርጉሙን ስላየነው መድገም ባያስፈልግም ቲቶ የተሰጠው ኃላፊነት ድርብርብ መሆኑን አንዘንጋ። ቅዱሳንን መምከርንም ቅዱሳንን ከእውነት መንገድ ሊያወጡና ሊያርቁ የሚወድዱ አሳቾችን መገሰጽንም የያዘ ነው።

<u>ገሰጽ፤</u> ገስጽ የሚለው ቃልም ከዚህ በፊት ሁለት ጊዜ ያየነው ቃል ነው። እዚያ መገሰጽ ሳይሆን መውቀስ ነው። በቲቶ 1፥9 *ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅሰ ይችል ዘንድ፥ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና።* በሚለው ውስጥ ሊወቅስ የሚለው ቃል ከመገሰጽ ጋር አንድ ነው። ማንን ሊወቅስ ተቃዋሚዎችን። እዚያ ለሽማግሌዎች ነው የተነገረው፤ እዚህ ደግሞ ለቲቶ ለራሱ። እዚያው ቲቶ 1፥13-14 *ይህ ምስክር እውነተኛ ነው። ስለዚህ ምክንያት የአይሁድን ተረትና ከእውነት ፈቀቅ የሚሉትን ሰዎች ትእዛዝ ሳያዳምጡ፥ በሃይማኖት ጤናሞች እንዲሆኑ በብርቱ ውቀሳቸው።* በሚለው ውስጥም በብርቱ መውቀስ የሚለው ቃል እዚህ ገስጽ ከሚለው አንድ ነው።

መገሰጽ ወይም መውቀስ ጥፋት፥ ስሕተት፥ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ያንን ለማስተካከል የሚደረግ ሂደት ነው። ከእውነት መንገድ ሊያወጡ ከሚወድዱ አሳቾችና ወደ ሕግ ጥበቃና በራስ ቻይነት ሊጸድቁና ሊድኑ ከሚያስተምሩና ከሚያስደርጉ ገያሪዎች ጋር የሚደረግ ፍልሚያም ነው። የቲቶ ተግባርና ኃላፊነት ሽማግሌዎችን ከመሾምና ቶሎ ከዚያ ስፍራ ከመራቅ ያለፈ ነው። እንዲያውም አንዳንዶቹ የተሰጡት ትእዛዞች እዚያው ሰንብቶ ነገሮችን አደረጃጀቶች፥ መልክ አስይዞ፥ አደላድሎ፥ ከርሞ ወደ ጳውሎስ እንደሚመለስ አመልካች ናቸው።

ማንም ኣይናቅህ፤ ከላይ እንዳየነው በሙሉ ሥልጣን እንደ ጳውሎስ እንደራሴ፥ ወይም እንደ ጳውሎስ እንደራሱ ሆኖ እንዲናገር የተነገረው፥ ሥልጣን እንደተቀበለ፥ ትእዛዝ እንደተሰጠው ሰው ሆኖ መናገር ያለበት ሰው ነው ቲቶ። ጳውሎስ ይህንን መጻፉ፥ ወይም ጠቅላላውን መልእክት መጻፉ፥ እርሱ ባይኖርም ልክ ጳውሎስ እንዳለ፥ ራሱ እያደረገ እንደሆነ ሆኖ እንዲሠራ ኃላፊነት ሲሰጠው፥ ቲቶ ቢሠራም ጳውሎስ የፈረመበት ጉዳይ መሆኑ እንዲታወቅ ነው። ስለ ቲቶ በመጀመሪያው ጥቅሶች ውስጥ ስንመለከት ማንነቱን በጥቂቱ ልናውቅ እስከሚቻለን ድረስ ኣይተናል።

ማንም ኣይናቅህ ያለው ምናልባት የሚንቁ ሰዎች ስላሉ ሳይሆን ኣይቀርም። የሚንቁ ሰዎች የሚንቁት ምናልባት ዕድሜው ታናሽ ስለሆነ ይሆን? ኣናውቅም። ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት ማንም ታናሽነቱን እንዳይንቅም ጽፏል፤ 1ጢሞ. 4፥11-12። ምናልባት በዕድሜው ካልሆነ በሥልጣኑ ሊሆን ይችላል። ከሆነ፥ ለዚህ ሳይሆን ኣይቀርም በሙሉ ሥልጣን፥ በድፍረት እንዲናገር ያሳሰበው።

የእውነት ጠላቶች የእውነትን ወዳጆች የሚመቱበት የመጀመሪያው መንገድ ንቀት ነው። የእውነት ወዳጆችን የሚንቁበት አንዱ መንገድ ራሳቸውን በማተለቅ ነው። ሌላው እውነተኞችን በማሸማቀቅ ነው። ጳውሎስ ቲቶን በዚህ መንገድ ንቅንቅ እንዳይል የተናገረው ማንም፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙት ሃይማኖተኞችም፥ ሥልጣን ናፋቂዎችም፥ የሐሰት ትንቢተኞችም፥ ማናቸውም እንዳይንቁት ነው።

ለውይይት

ጸጋ ምንድር ነው? ምንስ ማለት ነው? ጸጋው፥ 'ሰዎችን ሁሉ የሚያድን' ተብሎአል፤ ሰዎችን ሁሉ ያድናል? ወይም ሰዎች ሁሉ በጠቅላላ፥ በጅምላ ይድናሉ ማለት ነው? ይህ ጸጋ በዚህ ዘመን ኧንደት መኖር ኧንደሀብን ያስተምረናል፤ ምን ምን ያስተምረናል? ኧንደትስ ያስተምረናል?

መካድ ምን ማለት ነው? ባለማዊ ምኞትን መካድስ ምንድር ነው? ታላቁ ኣምላካችንና መድኃኒታችን የሚለው ቃል ከኣብና ከወልድ የተነገረ ነው? ወይስ ከኢየሱስ ብቻ? ኧንደት ኧናውቃለን? ነበሆነስ ነዚህ ምን ኧንማራለን?

የጌታን መምጣት መጠባበቅ በኣሁን ሕይወታችን ላይ የሚፈጥረው ለውጥ ኣለ? ምን? ኧግዚኣብሔርን መምሰል ምን ማለት ነው? ኧንድንመስለው የተሰጠን ሞይም ወይም ምሳሌ ኣለ? መቤዠት ምን ማለት ነው። ጌታ ኧኛን ኧንደት ነው የተቤዠን? ጳውሎስ ቲቶን ማንም ኧንዳይንቀው ለምን ኣደፋፈረው? ነዚህስ ምን ኧንማራለን?

ትምህርታዊ ጥያቄ 10፤ ጽኑት ያጠኳል ወይ? ጽኑት ክንጸሚጠኩና ያመኑ ለዎች ክንጸነካዱ የሚናገሩ ክፍኰችለ?

ክነዘህ ክሀሰት ወገናች የቀረቡ ጥያቄዎች ናቸው። ክንዱ ጠያቂ፥ ጽኑት ያጠኳል ወይ? የጻኑና ያመኑ ለዎች ኪክዱ ዯችካኩ ወይ? የሚል ነው። የሀሰተኛዋ ጠያቂ ጥያቄ፥ 'ክንጽ ክርለቲያን ከጻነ በሳካ የኪለገውን ቢያጸርግ ጽነቱን ኪያጣ ያችላል? ወይም ኪያጣ ለሰማያችል የኪለገውን ቢያጸርግለ?' የሚልና የተያያዘው ጥያቄ፥ 'ጽነቴ ኪጠኳ ለሰሚችል ክንጻያጠኳ ምን ማጽረግ ክሉብኝ?' የሚኩ ናቸው።

ጽነት ያጠኳል ወይ? የሚለው ጉጻያ ክሀሰት ነራ ካያ ተቁሞ የሚነበራነሩት ለነ ማዕከናታዊ ክርክር ብቻ ያማዕለክል። ግን ክያጸለም፤ ያህ ጉጻያ የየቀኑን ክማዕክለጎችንን ክና የክርለትና ክካሄጻችንን የሚነካ ጉጻያ ነው። ያህን ክጎብ በተማዕከነተ ሀሰት ነራዎች ክኩ።

ሀሰቱ ነራዎች

1. በክንጽ ነራ፥ ጥያቄው፥ 'ክንጽ ክርለቲያን ከጻነ በሳካ ጽነቱን ኪያጣ ለሰማያችል የኪለገውን ቢያጸርግለ?' ብለው የሚጠያቁና ክንጼ የጻነ ለሀኬ ጻነ ብለው የሚያለተምሩ ክኩ። ያህ፥ 'የኪለገውን ቢያጸርግ' የሚለው ሒሊግ ነው ጤናማ ክያጸለምም። 'ክንጼህ የሚኩት የጎጠኪክት የኪዎጽ ወርቀት ማላተም የሚኪልጉ ለዎች ናቸው። ጽኛለሁ፤ ጽጎንነቴ ክያጠኳም፤ ምንም ነገር ባጸርግ ያቅርታ የሚያጸርግልን ክምካክና ክባት ክለን የሚኩ ናቸው።

2. በኬለው ነራ፥ 'ጽነቴ ኪጠኳ ለሰሚችል ክንጻያጠኳ ምን ማጽረግ ክሉብኝ?' ብለው የሚጠያቁ ናቸው። 'ምን ማጽረግ ያሉብኝ?' የሚለው ጥያቄ ጸግሞ ለው ማጽረግ ወይም መሥራት ያለበትን ነገሮች የሚያመዕክነት በመዕሆኑ መጻንን የሥራ ውጤት የማጽረግ ጉጻያም ነው። መመበቅ ያሉብኝ ነገሮች ብለው ዝርዝር የሚያወጡ ለዎች ናቸው። ክነዘህ ክገኛነትን የሚነተኩ ለዎች ናቸው። በሥራ ወጸ መጻን የሚያጸኩ ለዎች ናቸው።

በሀሰቱም ክሳቦች ውለጥ ነቴክ ክውነት ክለ። ለክተትም ክለ፤ መጻናችን ክለመስጥቱ ክውነት ሊሆን ኃጢክት ለመሥራት ፈቃጽ መመዞቁ ለክተት ነው። የቅጽለና ክመዕክለ ናፍቆትን መናኒቅ ትነክክል ሊሆን መጻንን የሥራ ውጤት ማጽረግ ለክተት ነው።

መጻናችን ዘክለማዊ ነው፤ ኬል. 1፥3-14 ያህ ክውነት ነዓለም መቢጠር በቤት የታቀጸና የተኢጸመ መሆኑን ያናገራል። የታቀጸው-ም በክግዚክብሔር ነው፤ የተኢጸመው በክርለቶለ ነው።

በሥራችን ክያጸለም፤ ኬል. 2፥8-9 ጸጋው በክምነት ክጽናችኅነና፤ ያህም የክግዚክብሔር ለጦታ ነው ክንጼ ነክናገተ ክያጸለም፤ ማንም ክንጻያመዕካ ነሥራ ክያጸለም። ቲቶ 3፥5 *ክንጸ ምሕረቱ መመን ለለዲለ ልጸት በሚሆነው መታጠብና በመንቢለ ቅዱለ በመታጸለ ክጻነን ክንጼ፥ ክኛ ለካጸረግነው በጽድቅ ለለ ነበረው ሥራ ክያጸለም፤* ያሳል።

የጻንነውም ነጻነን በሳካ መጻናችንን የምንቢጽመውም በሥራችን ነሆነ ክንመዕካለን። ቁጥር 10 *ክኛ ፍጥረቱ ነንና፤ ክንመዕካለለበት ዘንጽ ክግዚክብሔር ለለቀጽም ያዘጋጀውን መልካመውን ሥራ*

ለማጽደግ በክርለቶለ ኪዮሉለ ተፈጠርን። ሊቅ ከጻን በሳካ የምንሠራው መልካም ሥራ ወንም ቲቶ 3÷8 የተጻፈው÷ *ክንሠዚክብሔርንም የሚያምኑት በመልካም ሥራ ለጥንቃቄ ክንጸደጹ÷* የሚከው የሚያሳየው ከመጻን በሳካ የሚታየውን ክንሠዚክብሔርን የሚያለክብርውን መልካመውን ሥራችንን ነው። *መልካመውን ሥራችሁን አያተው በለማያት ያለውን አባታችሁን ክንጸደያከብሩ ብርሃናችሁ ክንጸሀ በለው ፊት ያብሩ።* ማቴ. 5÷16። ያዕ. 2÷17-26 ክንጸሚነግርን ክምሳታችን በተግባር ካልታየ መጻናችንን ክውገልጥም።

በሥራ መጻንን ለመኪጸም የሚጸፈግ ጥረት ክርለቶለ በመለቀልክ ላው የኪጸመውና ተኪጸመ ያለበት ማጻን ያልተኪጸመና ክኛም የምንጨምርበት ነገር የቀረበት ነው የሚያለኝ ነው። ለመጻናችን ክንሠዚክብሔር የኛን ክንሠ ክልጠየቀም። ጸጋ ሊጸመር ሥራ ውሆናል መጻን ክልተባለም። ጸጋው በክምነት ክጽኗችሳል ነው የተባለው። ነዘህ ጋር የሚያያዘው ነጥብ÷ መጻናችን ሊጀመርም የኛ ያልሆነ የተለጠን ጽነት መለሆኑ ኪታወቀን ውገባል።

ኬላው መጻናችን በክንሠዚክብሔር የተጠበቀ ክንጂ በኛ ጥበቃ ለር ያለ ጉጻው ክውጸለም። ነለጠንም ሀኩ ክንጽን ለንኪ ክንጻላጠኬ በመጨፈርሻው ቀን ክንጻለነሣው ክንጂ የላነን የክብ ፈቃድ ውህ ነው። ዮሐ. 6÷39።

ጸግሞም በዮሐ. 10÷27-29 በነቼ ድምጿን ውለማኩ ክኔም ክውቃቸዋለሁ ውነተኩንማል፤ ክኔም የዘላለም ሕውወትን ክለጣቸዋለሁ÷ ለዘላለምም ክውጠኬም÷ ነነክጂም ማንም ክውሳጥቃቸውም። የለጠን ክባቴ ነሀኩ ውበልጣል÷ ነክባቴም ክጅ ኪሳጥቃቸው ማንም ክውችልም። ብኪል። በማጻን ብርቱ ብቻ ላውሆን በመጠበቅም ብርቱ መሆኑን የሚያላው ነው።

ዉሁ. 24-25 *ላቱለናነክኩም ክንጸጠብቃችሁ÷ በክብሩም ፊት በጸለታ ነውር የኬካችሁ ክጽርን ክንጸያቆማችሁ ለሚ ችለው ብቻውን ለሆነ ክምላክና መዴዎኒታችን ነዘላመን ሀኩ በቤቱ ክሁንም ክለነክ ዘላለምም ጽርለ በገለታችን በኪዮሉለ ክርለቶለ ክብርና ግርማ ኃያልም ሥልጣንም ያሁን፤* አሜን። ውላል።

ምንም ኪለዮን ክውችልም ክለ ጳውሎለምን፤ ሮሚ 8 35÷ *ነክርለቶለ ፍቅር ማን ያለዮናል? መነክሉ÷ ወያለ ጭንቀት÷ ወያለ ለጻት÷ ወያለ ሁብ÷ ወያለ ሁቁትነት÷ ወያለ ፍርሃት÷ ወያለ ለያፍ ነው?* 36÷ *ለለ ክንተ ቀኑን ሀኩ ክንገጸላለን÷ ክንጸሚታረዱ በጎች ተቆጠርን ተብሎ።* ክንጸ ተጻፏ ነው። 37÷ *በዘህ ሀኩ ግን በወጸጸን በክርሉ ነክለሸናል ዎች ክንበልጣለን።* 38÷ ሞት ቢሆን÷ ሕውወትም ቢሆን÷ መላክክትም ቢሆኑ÷ ግዘትም ቢሆን÷ ያለውም ቢሆን÷ የሚመጣውም ቢሆን÷ ኃያላትም ቢሆኑ÷ 39÷ ነበፍታም ቢሆን÷ ዝቅታም ቢሆን÷ ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርለቶለ ኪዮሉለ በገለታችን ላለ ነክክዘክብሔር ፍቅር ሊለዮን ክንጻዳዎችል ተለዳቼችለሀሉ። ክለ። ጥያቄው መለሆን ያለበት ኪለዮን ዎችካል ወያለ ክውችልም ላያሆን ነክክርሉ ጋር በፍቅር ውለጥ ነን? የሚለው ነው።

ጽነት ዉጠፍል ወያ? የሚለው ጥያቄ ሊቀርብልኝ በመጀመሪያ የምጠይቀው ጥያቄ ለውየው ሊጀመር ጽኗል ወያ? የሚል ነው። ብዙ ጊዜ የነውጹ ለዎችት÷ ነክክምነት ያኬንኬገ ወንም ክርለቶለን ነመመነተል ወዳ ሳነ ያኩ ለዎች ሊታይ ጥያቄዬ ቀጽሞ ጽነው ነበር? ምን ክርግመኛ ክጸፈገን ጽነው ክንጸነበር? የሚል ነው።

ማቴ. 7÷21-23 *በለማያት ያለውን የክባቴን ፈቃድ የሚያጸርግ ክንጂ÷ ጌታ ሆያ÷ ጌታ ሆያ÷ የሚለኝ ሀኩ መንግሥተ ለማያት የሚገባ ክያጸለም።* በዘያ ቀን ብዙዎች÷- ጌታ ሆያ÷ ጌታ ሆያ÷

በለምህ ትንቢት ክልተናገርንምን፦ በለምህለ ክጋንትን ክላወጣንምን፦ በለምህለ ብዙ ተክምራትን ክሰዳር ግንምን? ዓሡናክ። *ዮዚያን ጊዜም፦ ነቶ ክላወቅኳ ችሁምኟ ክናንተ ዓመፀኞች፦ ነክኬ ራቁ ብዬ ክመዕለክርገቸዋክሁ።* ዑካክ። ዲዳኑ ክPመዕለክኩ፦ ክርለቲያንኛ ክPተናገሩ፦ ጌታ ሆዑ ጌታ ሆዑ ክዩክ፦ ትንቢት ክPተናገሩ፦ ክጋንት ክያመጡ፦ ምክክቶችና ተክምራት ክያዪረጉ ያክዳኑ ሰዎች ኪናሩ ነቹክ፦ ‘ሊጃመርለ ጽሳው ሳበር ወዑ?’ ብኩ መመጦቅ ሕጋዊና ተገቢ ጥያቄ ሳው። Pክብን ፪ቃዪ ማዪርግና ኬኩች ሳገሮችን ማዪርግ Pተክያዩ ሳገሮች ናቸው። ዑህ ‘ማዪርግ’ ለክተዳሳ ክንጂ ክመዳን Pሚዪርግ ‘ማዪርግ’ ክክመዕሆኑን ክዑተናክ።

ጽሳት ክንዪሚጠኩና ያመኩ ሰዎች ክንዪሳካዱ Pሚናገሩ ክፍኩችለ?

Pካዱ ሰዎች መናሮራቸውን Pሚናገሩ ምንባቦች መናሮራቸው ግክጽ ሳው። ክምላኬ፦

1ጢሞ. 1፥18-20 *ጢሞቴዎለ ክጂ ሆዑ፦ ክለቀዪግሞ ለክ ክንጸ ተነገርው ትንቢት፦ በነርሱ መክነካግሞ ጦርነት ትዋጋ ዘንዪ ዑህችን ትክዘዝ ክዪራ ክለጥሄክሁ፤ ክምኖትና በጎ ሕሊና ዑኩርህ፦ ክንጸንዪች ሕሊናን ጥክው፦ መርነጡብ ክክ መሪ ክንዪሚጠኩ፦ በነክምኖት ነገር ጠፍተዋክናና፤ ነክነሃዚያም፦ ክንጸዑሳዪቡ ዑማሩ ዘንዪ ክለዑጣን ክላክጌ። Pለጠኳቸው፦ ሄሜኔዎለና ክለነክንዪሮለ ናቸው።* ክንዱ ሳው። ክነዘህ ሰዎች ያምኑ Pነበሩ ሰዎች ናቸው። ሰዎች ነክክምኖት ኪንሸሁተቱ ክንዪሚችኩ ጴጥሮለ መናካዱ ዩላPናክ። ነክ12ቱ ኬላም Pካዱ ክክ፤ ዑሁዳ። ዑሁዳ ግን ነጅምሩም ያመነ ክክመዕሆኑን ሚረጋገጥ ክንችካክን። ክዘህ ሳው ሊጃመርለ ጽኖ ሳበር ወዑ? ብኩ መመጦቅ ተገቢ Pሚሆነው። ጴጥሮለ መመዕክሩና ንለሐ መግባቱ ርቆ ያክመዜዱ መሆኑን ክና ወዪቆ መነሣት መናሮን ያመዕክናታክ።

ክዪው ርቀው Pሚዜዱትንና በዘያው Pሚጠፉትን፦ በተክዑም Pክነህዪት ትምህርት ክካዚያጀች Pሆኑ ሰዎችን ለናለብ 1Pሐ. 2፥19 *ነክኛ ዘንዪ ወጡ፦ ዳሩ ግን ነክኛ ወገን ክልነበሩምኟ ነክኛ ወገንለ ቢሆኑ ነክኛ ጋር ጸንተው በነሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁኩ ነክኛ ወገን ክንዪልሆኑ ዑገክጡ ዘንዪ ወጡ።* Pሚክው ክውነት ግልጥ ዑሆናክ። ወጡ፤ ክማን ወጡ? ቀዪሞም ወገን ክክመዕሆናቸው ዑገክጥ ዘንዪ ወጡ።

ለክዚህ Pካዱ ሰዎችን ለናለብ ሁክት ጥያቄዎችን ክንገበዑቅ። 1ኛ፦ ቀዪሞ ክምሳው ሳበር ወዑ? Pዑሁዳ ዓዑነት ኪሆኑ ክዑችኩም ወዑ? 2ኛ፦ Pጴጥሮለ ዓዑነቶች ነሆኑና በሕዑወት ነናሩ ነክክክዪታቸው ኪመዕክሉ ክዑችኩም ወዑ? ክሁን ያኩበት ሁኔታ Pመጨረሻቸው ሳው ወዑ? Pመጨረሻቸው ለክመዕሆኑለ ክርግመኛ መሆን ክንችካክን ወዑ?

ክንዪንዪቹ ነሐዲዎች መምመዕክለ ክንዪማዑችኩ Pሚናገርባቸው ምንባቦችም ክኩ። ክምላኬ፦ ዕብ. 6፥4-6 ክንዱ ሳው።

መቅካካ Pመጽሐፁን ክሳብ ነማዎታችን በኬት ዑህንን Pምዕራፁን ክቀማመጥ ነናመጊን። 6፥1-3 ጳውሎለ ራሱንም ጨምሮ፦ ‘ነኛ’ ነያክ ለክማዪግ ሳው Pሚናገርው። 6፥4-8ን ክልኬን ነቁጥር 9 ‘ነናንተ’ ነያክ ለክ ክነርሱ ለክ ዕብራውያን ሰዎች ሳው Pሚናገርው። በመነካከል ባክው ነቁጥር 4-6 ባክው ክፍክ ግን ለክክነሃዚያ ሰዎች ዑናገራክ። ቁጥር 7-8 ዪግሞ በምለክ Pነዘህ ሰዎች ፍጻሜ ተገልጠክ።

ወዳ ጠቅላላው ፆዕብራውያን መጽሐፍ ኀና ተቀባዮች ለንመኮጣ ዳግሞ ጠቅላላው መጽሐፍ ፆተጻፈው ለዕብራውያን ወንዎም ኣንሁድ ክርለቲያናዮች ነው። ኀነዚህ ለዎች ወዳ ክርለቶለ ኀምነት ፆመጡ ኣንሁድ ናቸው። ፆብኩዎ ኪዳን ኀውቀት ያላቸው÷ ታሪካቸውንም÷ ፆሃዎማኖታቸውን ሥርዓትም ጠንቅቀው ፆሚያውቁ ናቸው። ማመቅ ብቻውን ቦቂ ኣለመሆኑን ማለተዋል ኣለብን። ማመን ኀማመቅ ፆሚበልጥ መሆኑን ማለተዋል ኣለብን። መልክኀክቱ ፆተጸገፀው ማለጠንቀቂያዎችን ዎናገሩልኧ

ፆመጸመሪያው ማለጠንቀቂያ ዎህን ታካቅ መጻን ፆተባለውን ጽነት ቸል ያኩ ለዎች መናሮቸው ነው፤ ዕብ. 2÷1-3። ዎህ ፆዕብራውያን መልክኀክት ኣለቀጽሞ ኣጉ በመኮኀክት መኮኀበክኛነት ፆተለጣቸውና ቸል ያኩት ኀተቀጡ÷ ኀመኮኀክት በሚበልጠው በክርለቶለ ፆተገገርውን ቸል ማክት ዎበልጥ ፆሚያለቀጣ መሆኑ ነው ማለጠንቀቂያው። ለዚህ ቸልተኞች ፆሆኑ ለዎች መናሮቸው ዎታያል።

ሀለተኛው ማለጠንቀቂያ ዳግሞ መሁሌን ኀክርለቶለ ጋር በማነጻጸር÷ ኣነዚህን ኣዎሁጻውያን ክርለቲያን ለዎችም ኀግብጽ ኀመጡት ኣዎሁድ ጋር በማነጻጸር ክልና ፆሚያምን ልብ ያላቸውና በኃጢኣት መታለል ኣልኀኛ ፆሆኑ ለዎች መሆናቸውን ዎገልጣል፤ ዕብ. 3÷12-19። ኀግብጽ ፆመጡት ለዎች ያልገቡት ባለማመናቸው ጠንቅ ነበር። ወጥተዋል፤ ኣማኞች ዎመለለከ፤ ግን ፆሚያምኑ ለዎች ነበሩ።

ሦለተኛው ማለጠንቀቂያ ዕብ. 6÷4-6 ነው፤ ዎህን ዎላል፤

4÷ *ኣንድ ጊዜ ብርሃን ፆበራላቸውን ለማያዊውንም ለጦታ ፆቀመሱትን ኀመንፈለ ቅዱለም ተካፋዮች ፆነው ፆነበሩትን÷* 5÷ *መልካመውንም ፆኣግዚኣብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃያል ፆቀመሱትን÷* 6÷ *በሷላም ፆኣዱትን ኣንደገና ለንለሐ ኣነርሱን ማዶለ ፆማያቻል ነው፤ ለራላቸው ፆኣግዚኣብሔርን ልጅ ዎለቅኩታልና ያዋርዱትማልና።*

ዎላል። ኣዚህ ፆተጠቀሱት ምላት ትልልቆችና ኀባዶች ናቸው። ፆበራላቸው፤ ፆቀመሱት÷ ተላፋዮች ፆሆኑት ፆሚኩ ናቸው። ጥያቄው ኣነዚህ ልምምዶች ፆጽነት ልምምዶች ናቸው ወዎለ ኩጽነት ትንሽ ገዳዎ (ሩብ ገዳዎ÷ ኣምለት ገዳዎ ኣንደምንሕው) ኩጽነት ትንሽ ፆቀርው÷ ኀጽነት ፆንጹኩ ልምምዶች ናቸው?

ጥያቄው ወዎም መመጦቅ ያለብን፤ በራላቸው? ወዎለ ራላቸው ብርሃን ሆኑ? ነው ጥያቄው። ቀመሱ? ወዎለ ፆቀመሱትን÷ ያጣመመትን በኩት? ነው ጥያቄው። መቅመለ መብላት ኣለመሆኑን ኣናውቃለን። ኀመንፈለ ቅዱለ ተላፋዎ ሆኑ? ኣንዴት ነው ተላፋዎ ፆሆኑት? በማመን ነው? ወዎለ መንፈለ ቅዱለ ባመኑት ለዎች ኣማላዎነት ባለመኑ ለዎች ዘንድ ፆሚሠራውን ሥራ ተላፋዎ በመሆን ነው? ዮሐ. 16÷8 ላዎ÷ *ኣርሱም መጥቶ ለለ ኃጢኣት ለለ ጽድቅም ለለ ፍርድም ዓለምን ያወቅላል፤* ፆሚለው በመለማመድ ነው ተላፋዎ ፆሆኑት? ወዎለ መንፈለ ቅዱለ በኣነርሱ ውለጥ መናሮ ጸመር?

ቁጥር 7-8 ላለው ኀፍርዱ ወዎም ኀቅጣቱ ጋር ሊተያዎ ኣነዚህ ለዎች ኣሾህና ኩርንችት ኀምዕዋጣ መሬት ጋር ነው ፆተነጻጸሩት። ኀክርለቲያናዊ ባህርዎ ጋር ኣብሮ ፆማዎሄድ ውጤት ነው ፆተመዘገበው። 7÷ *ብዙ ጊዜ በኣርለዋ ላዎ ፆሚወርደውን ዝናብ ፆምትጠጣ መሬቱ÷ ለሚያርሱለትም ዳግሞ ፆምትጠቅምን ኣትክልት ፆምታበቅል÷ ኀኣግዚኣብሔር ቢረካትን ታገኛለችና፤*

8፥ ክርህና ኀዙረንችትን ግን ብታወጣ፥ ቦተጣለችኝ ናት ለመቢገመም ትቀርባለችን፥ መበጨቢጣዋም መውጣለ ነው።

ኪሳ. 5 ውስጥ ቦተጻቢውን ቦወጉን ተኳለ ቦሚመስለ ነው። *ወጉንን ያቢራለ ብዙ ለትማመን ለለ ምን ሆምጣ ፍሬ አለራ? . . . ባጽማ አጸርገዋለሁ፤ አጉቋጥም፥ አጉኰተኰትም፤ ኀዙረንችትና ክርህ ጉበቅለበታለ፤* (ቁ. 4 ኳና 6)። ክርህና ኀዙረንችት ቦመጥጣልና ቦመትተው፥ ወናና ባጽማ ቦመሆን፥ ባለቤት ቦኤለው ቦመሆን ምልክት ነው። ለለዚህ ቦተጣኩ፥ ቦማንም ያልሆኑ ለዎች መመሆናቸውን ያሳያል።

ኳራተኛው ማለመንቀቂያ ዕብ. 10፥26-31 ጉገኛል። ንጽጽሩ ቦመሌን ሕግ መጣል ኳና ኣዲሱን ኪዳን መጣል ነው። ቦኳውነትን ኳውቀት መቀበል፥ ወጽዶ ኃጢኣት ማጽቢግ፥ ኰዘያ ቦኳግዚኣብሔርን ልጅ መርገጥ፥ ቦተቀደሱበትን ቦኪዳን ደም ኳንጹ ርኩለ መቁመር፥ ቦጸጋውን መንፈለ ማኳኳት ቦሚኩ ትልልቅ ሾካት ተጽቂውበታል። ኳዚህም መመጠቅ ያለብን ቦምር ጥያቄዎች ኳኩ፤

ጥያቄው፥ ሊጾመር ቦኳውነትን ኳውቀት ተቀብለውት ነበር ወጉ? መቀበል በተቀበኩት መኖርን ያመለኳታል፤ ኳና በተቀበኩት ቦኳውነት ኳውቀት ኖሩበት? ወጉለ ኣልናሩበትም? ጥያቄው፥ ወጽው ኃጢኣት ማያጸርጉ ኰሆኑ፥ ኃጢኣት ሁኩ ወጽው ቦማያጸርጉት ነገር ነው። ጉህ ኳዚህ ቦተገመመው ግን ኰኃጢኣቱ ባሻገር ቦተጺገ ነገሮችም ለኳኩ ጸርገቱን ብቻ ላጉሆን ቧልብን ሁኔታም ማያሳጉ ነው። ጥያቄው፥ ጉህንን ቧጊጠትን ወጉም ማጊግጠትን ቦኳግዚኣብሔርን ልጅ ተቀብለውት ነበር ወጉ? ቦሚለው ነው። ጥያቄው፥ በዚህ፥ 'ቦተቀደሱበትን ቦኪዳን ደም' በተባለው ተቀጽሶው ነበር ወጉ? ተቀጽሶው ቦቅጽለናን ነገር ኪለማመጹ በመኪዘግ ፈንታ ኳንዴት ወጽው ኃጢኣትን ጉለማመጸኩ? ጥያቄው፥ ቦጸጋውን መንፈለ ማኳኳት መንፈለ ቅዱለን ማኳኳት ኣጉደለም ወጉ? ኳነዚህ ነገሮች ቦዳነ ሶው ምልክቶች ናቸው ወጉ? ቦጸጋውን መንፈለ ማኳኳት መንፈለ ቅዱለን ማኳኳት ኣጉደለም ወጉ? መንፈለ ቅዱለን ማኳኳት መንፈለ ቅዱለን መለጸብ ኣጉደለም ወጉ? መንፈለ ቅዱለን መለጸብ ኳርለቶለን ኣለመመቀበል ኣጉደለም ወጉ?

ኰጥያቄዎቹ ጋር ተያይዞ ኰዕብ. 10፥32-39 ኳንጸምንጊጻው ኳነዚህ ሶዎች ቦኳምነታቸው ምኳንያት ለጸት፥ መኰራ፥ ንጥቂያና ኳለራት ኳቦተቀበኩ ያኩ ሶዎች ናቸው። ኰዘህ ቦተነሣ በመጽናት ቦቆዎ ኣማኞች ኣኩ፤ ኳያጊጊጉ ያኩም ኣኩ። ኳያጊጊጉ ያኩት ሁኔታውን ኣያተው ቦሚኰተኩ ኳንጺ ቦኳምነታቸውን ራለና ጊጸሚውን ተመልኳተው በጌታቸው ያለውን ሩጫ ቦሚርጡት ኣያጸኩም። ቁጥር 38-39 *ጻድቅ ግን በኳምነት ያናሮል ወጸ ሷካም ቢያጊንግ፥ ነፍሴ በኳረሱ ጸለ አያሳትም። ኳኛ ግን ነፍሳቸውን ሊያጽሩ ኰሚያምኑቱ ነን ኳንጺ ወጸ ጥፋት ኰሚያጊንፉ አያጸለንም።* ቦሚለው ቦለዎቹን ማንነት ቦሚገልጥ ነው። በኳምነት መኰራን ኳቦተቀበኩ ቦሚናሩ ቦሚጾሩ ኣኩ። ኳንጸ ጻጽቅ በኳምነት ቦማያናሩና ወጸ ጥፋት ኳያጊጊጉ ያኩ ጸግሞ ኣኩ።

ኰለያ ኳንጸልኰትት፥ ጽነት ያጠኳል ወያ? ቦሚለው ጥያቄ ሊቀርብልኝ በመጺመርሀያ ቦምጠያቀው ጥያቄ ለው-ቦው ሊጺመር ጽኗል ወጸ? ቦሚል ነው። ብዙ ጊዜ ቦኳጹ ሶዎች፥ ኰኳምነት ያጊጊጉ ወያም ኳርለቶለን ኰመኰተል ወጸ ሷካ ያኩ ሶዎች ሊታይ ጥያቄይ ቀጽሞ ጽነው ነበር? ምን ኳርግጠኛ ኣጸሊገን ጽነው ኳንጸነበር? ቦሚል ነው።

ትምህርታዊ ጥያቄ 11፤ ኳውሃተኛ መጻን ዖታወቃክ? ሚፒጋገጫውለ ምንጽን ሃው? በምን ኳናውቃክን?

መጻን ዖታወቃክ። ኮሚታወቅባቸው መክኪያዎች መኮኮክ ጥቂቱ ኳሃዘህ ናቸው።

1. ኪPሉለ ሬታ ኳንጸሆሃ መመመለኮርና መታመን፤

ሮሚ 10÷9-10 *ኪPሉለ ሬታ ኳንጸ ሆሃ በአፍህ ብትመለኳር ኳግዚአብሔርም ኮመሙታን ኳንጸለነሣው በልብህ ብታምን ትጽናክህና፤ ለው በልቡ አምኖ ዖጸጽቃክና በአፏም መለኳር ዖጽናክና።* ማመንና መመመለኮር።

1Pሐ. 4÷14-15 *ኳኖም አዖተናክ አባትም ልጆን Pዓለም መጽኃኒት ሊሆን ኳንጸ ሳኮው ኳንመለነኳሁን። ኪPሉለ Pኳግዚአብሔር ልጅ ኳንጸ ሆሃ በሚታመን ሀሉ ኳግዚአብሔር በኳርሉ ዖናሃክ ኳርሉም በኳግዚአብሔር ዖናሃክ።* ዖክል። መመመለኮርና መታመን። ዖህ Pመጸመሀያው ኳርምጳ ነው። Pልብ ኳምነት÷ Pኳፍ ምለኳርነት። ብዙ ጊዜ ለዎች ወጸ ኳምነት ሊመጡ በአጸባባዎ በመጽዲኳ ኳንጺመለነኳሉ Pሚጸዲገው ለዘዘህ ነው።

1Pሐ. 5÷10 *ክርለቶለ ሃው ብኩ በኪPሉለ Pሚያምን ሀሉ ኮኳግዚአብሔር ተመክጸኳክ፥ መኳጀንም Pሚወጽ ሀሉ ኮኳርሉ Pተመክጸውን ጸግም ዖመጻክ።* ዖክል። ኳርለቶለ ነው ብኩ በኪPሉለ ማመን።

2. ኳርሉን መታዘዝና በኳርሉ መኖር፤

1Pሐ፣ 5÷2-3 *ኳግዚአብሔርን ለንመጽ ትኳዘዘቱንም ለናጸርግ Pኳግዚአብሔርን ልጆች ኳንጽንመጽ በዘህ ኳናውቃክን። ትኳዘዘቱን ልንጠብቅ Pኳግዚአብሔር ፍቅር ዖህ ሃውና፤ ትኳዘዘቱም ኮገጸች አዖጸኩም።* መታዘዝ Pመጸናችን ምክኳት ነው። ኳንጻንጸች ትኳዘዘቱን ኳንጸሚቲልገ በመኮኳቲክ Pሚመጺቸውንና Pማዖመጺቸውን በመኮክቲክ ገሚሉን ዖታዘዘኩ፤ ገሚሉን ዖተዋኩ።

Pሐ 14÷15 *ብትመጹኝ ትኳዘዜን ጠብቁ።* ዖክል። Pመመውጸትን ኳንጽ መቲተኛ ትኳዘዘቱን መመበቦችን ነው። Pማትመጻቸው ትኳዘዘት ኮኖሉለ ምን ታጸርጋክህ? መክሉ ቀካል ነው። ውጸጻቸው። Pተሳሳትኮው ኳንተ ሃህ ኳንጺ ዎኩ አዖጸክም። ኮዎኩ ጋር በመጸሁጸር Pሚለማመሙኝና Pማዖለማመሙኝ፥ Pምመጻቸውና Pማክመጻቸው፥ Pምታዘዘቸውና ያክታዘዘቸው ክትክ ኳክተቲቀጸክህም። ዎኩ ኳጽርጽር ኳክቀቢበም።

ኳርሉን መታዘዝና በኳርሉ መኖር ኳርሉን መመውጸጽ ነው። ኳርሉን ለንመጽጽ ኳርሉን ለኳመጸጽን Pምንመኮው ኳካ ኳክ።

3. ኃጢኳትን መዋኳት ኳና ኮሉዖጣን መኮራቅ

ኃጢኳትን ታጸርጋክህ? ኃጢኳት ያለጸለትሃክ? በኃጢኳት ትኖራክህ? በኃጢኳት ሁለህን ለታገኝ ጸለ ዖክሃክ መዖለ ትቢበኛክህ? ኃጢኳት ያለጸለትሃክ መዖለ ያለጠንቅሃክ? 1Pሐ. 3÷9 *ኳግዚአብሔር Pተመክጸ ሀሉ ኃጢኳትን ኳያጸርግም፥ ዘሩ በኳርሉ ዖናሃክና፤ ኮኳግዚአብሔርም ተመክጸኳክና ኃጢኳትን ሊያጸርግ ኳዖችልም።* በኃጢኳት ኳያጸርግም ኳና ሊያጸርግ ኳዖችልም Pቀጣዖ ጽርጊት

ግሦች ናቸውና የማዳረግ ልምድን የሚያመለክቱ ናቸው። በጎጠኝነት የመናፍርን ሁኔታ ከመልካካች ናቸው። በጎጠኝነት የምንጸለት ከሆንን ቅር የማንለኝ፥ የማንጸጸት፥ የማፍቅረቂረን፥ የማንነስቅ፥ የማንጨነቅ ከሆንን የቅዱሱ ክምካነ ዘር በውለጣችን የለም። ጎጠኝነት ክድረን ምንም ክንደካደረግሁ፥ ምንም ክንደልተዪጠረ፥ ሆኜ የምቀኖል ከሆንኩ ክልዳንኩም። ጸጸት፥ ሳዘን፥ መነስኴት፥ መቅሸሽ፥ ማዳፍ ከተለማኝ ግን ያ የመዳኔ ምልክነት ነው። ቅድለናን መዪለግ የሚርበንና የሚጠማን ከሆንን የመዳናችን ምልክነት ነው። ንጽሕናን የምንዪልግ ከሆንን ወዳ ቆሻሻው የሚመለስ ኩሪያ፥ ወዳ ትኴቱ የሚመለስ ውሻ ያለመሆናችን ምልክነት ነው።

ከለዮጣን መስራቅ ለንልም ነዚህ የተያያዘ ነው። ነነክፁው፥ ከለዮጣን ግዛት በመስራቅ ራሳችንን ኣንመጠብቃለን? ነነኣግዚአብሔር የተወለዳ ሀሱ ጎጠኝትን ባለመሥራት ራለን ከለዮጣን፥ ነነክፁው ዪመጠብቃልኴ 1ዮሐ. 5፥18 *ነነኣግዚአብሔር የተወለዳ ሀሱ ጎጠኝትን ኣንዳያደርግ፥ ነገር ግን ነነኣግዚአብሔር የተወለዳው ራሱን ኣንዲጠብቅ ክፁውም ኣንዳዪነካው ኣናውቃለን።* ዪካል።

ዪህ ማለት ራሳቸን የራሳችን መባቂና ኣዳኝ ነን ማለት ኣዪደለም። ያዳነን ጌታ ነው። ዪህ ለለ መዳን መናገሩ ሳዪሆን ግን ነበዳንን በሚነ ራለን ለለመመጠበቅ ነው። ሆን ብለን ነነኣንዳንድ ለዎች፥ ነነኣንዳንድ ትምህርቶችና ኣለተማሪዎች፥ ነነኣንዳንድ ቦታዎች፥ ነነኣንዳንድ የሚታዪና የሚደመጡ ነገሮች ራሳችንን ኣናርቃለን። ኣነዚያ ነገሮች ለዎጣን ኣንድንዪተንና ኣንድንመድቅ የሚጠቀምባቸው መሣሪዎች ናቸው። ዳግም የተወለድን ከሆንን ነመሣሪዎቹ ራሳችንን ኣናርቃለንኴ ኣንጠነቀቃለን። ጠባቂ ኣለንና ብለን ወዳ ቲተና ራሳችንን ኣንነትም።

4. ፍሬ ማፍራት የመዳናችን ምልክነት ነው።

ዮሐ. 15፥4 *በኣኔ ኑሩ ኣኔም በኣናንተ። ቅርንጫፍ በመዪኑ ግንድ ባዪኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ ኣንዳዪቻለው፥ ኣንዲሁ ኣናንተ ዳግም በኣኔ ባትኖሩ ኣትችሉም።*

የዘሁውን ምላኬ ኣንመሉስኴ ማቴ 13። የኣራቱ ዘሮች ኣመዳዳቅ ዪገልጠዋል ኣማንን። የመጀመርያው የመብቀል ዕድል ኣንኪ ኣላገኘም። ሦስቱ ግን በቅለዋል። ነከሦስቱ የመጀመርያው በጭንጫ መርሬት ላዪ የመዳቀው ነው። መዳያው በቀለ። ዪህ ለው ምን ዓዪነት መሆኑን ጌታ ሊናገር ኣንዲህ ኣለ፤ *በጭንጫ ላዪ የተዘራውም ዪህ ቃሉን ለምዶ መዳያው በዳለታ የሚቀበለው ነው፤ ነገር ግን ለጊዜው ነው ኣንጂ በኣርሱ ሥር የለውም፥ በቃሉ ምክንያትም መነስ መዪም ለዳት በሆነ ጊዜ መዳያው ዪለናነካል።* ማቴ. 13፥20-21። ለሚታዊነት ኣለበት። ዳለታ ኣለበት። መንጂላዊነት ግን የለበትም።

ሀለተኛው በኣሾህ መነሳነል የመዳቀው ነው። ዪህኛው ምን ዓዪነት ለው መሆኑን ሊናገር ጌታ ዪህን ኣለ፤ *በኣሾህ መነሳነል የተዘራውም ዪህ ቃሉን የሚለማ ነው፥ የዘህም ዓለም ኣሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ዪሆናል።* ማቴ. 13፥22። ኣዘህ ዓለማዊነትና የሥጋዊነት ምኞት ኣል ኣንጂ መንጂላዊነት የለም።

ሦለተኛው በመልካም መርሬት የመዳቀው ነው፤ *በመልካም መርሬት የተዘራውም ዪህ ቃሉን ለምዶ የሚያለተውል ነው፤* ኣርሱም ፍሬ ያፈራል ኣንዱም መቶ ኣንዱም ለዳሳ ኣንዱም ሠላሳ ያፈርጋል። ማቴ. 113፥23። ሥራ ኣያድነንም መዳናችንን ግን ያረጋግጣል። ፍሬ መዳናችን የሚታዪበት ዋና ምልክነት ነው።

ከነዚህ ጥቂቶች የመጻን ምልክቶች ናቸው። የኢየሱስን የማድሊግ ጥያቄ ከና ክንዴ ጽኛለሁ ለሁሌም ጽኛለሁ የሚለው ክባባል ሉንጢክ ፈቃድ መመጦዋቂያ ማመዛልከቻ ነበሩ የመጻን ምልክት ክዖዳለም። የኢየሱስን ማድሊግ ከና ጸቀ መዝመዙርነት ክብሊው ክዖሌዱም። መጻን ጸግሞ÷ ጽነው ወዲያውኑ ካልሞቱ በቀር÷ ጸቀ መዝመዙርነት የሚኩትን ኍክፌነት የያዘ ነው። ጸቀ መዝመዙርነት በትርጉመ በኩቃ. 9÷23 *ለሁኩም ክንዲህ ክሳቸው÷ በኒካዬ ሊመጣ የሚወዶ ቢኖር÷ ራሱን ዖካዶ መለቀኩንም ዕክቱ ዕክቱ ተሸክሞ ዖከተክኝ።* ተብሎ ክንዶተጻፈው መነካዶ ክለበት÷ መሸነከምና መነከተልም ነው።

መነካዶ ካለ የኢየገውን ብሎ ነገር ክዖሠራም። መነካዶ ካለ ራስ የራስ ክዖዳለም ማለት ነው። ራስ ተክዶ ለኬላ ተለጥቷል ማለት ነው። ባለቤት ክለ ማለት ነው።

መሸነከም ካለ÷ የሚሸነከመት በግልጽ ተነግሯልኔ መለላቀል ነው። መሸነከም ካለ ሞት ክለበት ማለት ነው። መሸነከመም ዕለት ዕለት ነው።

መነከተል ካለ ነቤት የሚያዩት ሞዴል ክለኔ የሚኬዶበት ቦታ ክለኔ መጽሊሻ ክለኔ ግብ ክለ ማለት ነው። መጻን ክው-ነተኛ ነበሩ ክዖጠኩም። ክው-ነተኛ መሆኑን ግን ክርግጠኛ ልንሆን ያሻል። ክው-ነተኛ መሆኑ ጸግሞ ዖታወቃል።

ነጥያቄዎች

ለውይይት

ከላይ ነተጠቀሱት ጥያቄዎች የሽናንነተም ጥያቄ በሆኑት በጥቂት ሰዓቦች ላይ ተወያዩ።

ድነት ይጠፋል ወይም ሊይጠፋም የሚሉት ሰዎች ተግባራዊ ጉዳዮች ምን ይመስሊችኋል?